…ዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሳይንስና ከፍተኛ የትምህርት ሚኒስቴ…
ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of science &higher Education
Debre Markos University


# የጨረታ ማስታወቂያ
## ብግጨ 27/2015

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2015 የበጀት ዓመት ከመንግስት በተመደበለት በጀት ለ2 አመት የሚቆይ የባነርና ስቲከር ህትመት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል። ስለሆነም በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ ከዚህ በታች ማለትም፡-

1. በዘመኑ የታደሰ ንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቲን ምዝገባ የምስክር ወረቀት ከሚመለከተው የመንግስት አካል ማቅረብ የሚችሉ፣
2. የጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ብር 50,000.00/ሀምሳ ሽህ/ ብር በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም አሠርተው ማቅረብ ሲኖርባቸው በጥቃቅን የተደራጁ ከአደራጃቸው የመንግስት መ/ቤት የዋስትና ደብዳቤ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም በማሠራት ማቅረብ የሚችሉ፣
3. አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ በተገለፀለት ከ7/ሰባት/ ተከታታይ የሥራ ቀናት በኂላ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝ በ8 ቀናት ውስጥ ውል መያዝ የሚችል መሆን አለበት፣
4. ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች ሁሉ የጨረታ ዶክመንቱን ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 እና አዲስ አበባ አራት ኪሎ ከቅድስት ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ወረድ ብሎ ሮሚና ካፌ ህንፃ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 07 ድረስ በመቅረብ ማስታወቂያው <u>በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ</u> <u>ለተከታታይ 15 ቀናት</u> የማይመለስ ብር 200.00/ሁለት መቶ/ በመክፈል ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፣
5. ተወዳዳሪ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ በመሙላትና በማሸግ <u>በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡59 ድረስ</u> ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ድረስ በመቅረብ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፣
6. ጨረታው <u>በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00</u> ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት <u>በዚሁ ቀን ከጠዋቱ 4፡30</u> በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 በግዥ ቡድን ቢሮ ቁጥር 10 ይከፈታል። ሆኖም ተጫራቾች በጨረታው ላይ መገኘት ካልቻሉ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ በጨረታው ላይ ያልተገኙ ተጫራቾች ፖስታን ጨምሮ ጨረታው በእለቱ ይከፈታል።
7. የጨረታውን ፋይናንሽያል ኦርጅናል ዶክመንቶች እንዲሁም የጨረታ ማስከበሪያውን ለየብቻ አስተማማኝ በሆነ ማጣበቂያ በታሸገ ፖስታ በማድረግና በእያንዳንዱ ፖስታ ላይ የመ/ቤቱን ሙሉ ስምና አድራሻ በመፃፍ ማህተም በማድረግ በተጠቃለለ አንድ ፖስታ በማሸግ ማቅረብ ይኖርባቸው።
8. ዩኒቨርሲቲው ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

<u>ማሣሰቢያ</u>፡- የጨረታ መዝጊያና መክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም በበዓል ቀናት ከሆነ ጨረታው በቀጣዩ የሥራ ቀን ተዘግቶ የሚከፈት ይሆናል።

ለበለጠ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር 058-771-66-91 ደብረ ማርቆስ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

Debre Markos University Procurement Administration Process No 1